# ሌሎች የአምላክን ፈቃድ እንዲያደርጉ መርዳት

***ስለ ተማርካቸው ነገሮች ለሌሎች መናገር የሚኖርብህ ለምንድን ነው?*** (1)

***ምሥራቹን ለእነማን ማካፈል ትችላለህ?*** (2)

***ጠባይህ በሌሎች ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል?*** (2)

***ከጉባኤው ጋር በስብከቱ ሥራ ልትካፈል የምትችለው መቼ ነው?*** (3)



1. እስከ አሁን ብዙ ጥሩ ነገሮችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሳትማር አልቀረህም። ይህ ያገኘኸው እውቀት ክርስቲያናዊ ባሕርያትን እንድትከተኩት ሊያደርግህ ይገባል። (ኤፌሶን 4:22-24) እንዲህ ያለው እውቀት የዘላለም ሕይወት ለማግኘት የግድ አስፈላጊ ነው። (ዮሐንስ 17:3) ይሁን እንጂ ሌሎች ሰዎችም ሕይወት እንዲያገኙ ምሥራቹን መስማት ያስፈልጋቸዋል። እውነተኛ ክርስቲያኖች በሙሉ ለሌሎች ሰዎች መመስከር ይኖርባቸዋል። ይህ የአምላክ ትእዛዝ ነው።— ሮሜ 10:10፤ 1 ቆሮንቶስ 9:16፤ 1 ጢሞቴዎስ 4:16



2. የምትማራቸውን መልካም ነገሮች በአካባቢህ ለሚገኙ ሰዎች በመናገር ምሥክርነት መስጠት ትችላለህ። ለቤተሰቦችህ፣ ለወዳጆችህ፣ ለትምህርት ቤትና ለመሥሪያ ቤት ባልደረቦችህ ተናገር። ይህን በምታደርግበት ጊዜ ደግና ታጋሽ ሁን። (2 ጢሞቴዎስ 2:24, 25) ሰዎች አንድ ሰው ከሚናገረው ነገር ይበልጥ የሚያደርጋቸውን ነገሮችና ጠባዩን እንደሚመለከቱ አስታውስ። ስለዚህ የምታሳየው ጥሩ ጠባይ ሌሎች ሰዎች የምትናገረውን መልእክት እንዲያዳምጡ ሊያደርጋቸው ይችላል።— ማቴዎስ 5:16፤ 1 ጴጥሮስ 3:1, 2, 16

3. ከጊዜ በኋላ በአካባቢህ ካለው የይሖዋ ምሥክሮች ጉባኤ ጋር ተሰማርተህ ለመስበክ ብቁ ትሆናለህ። ይህ በጣም አስፈላጊ የሆነ እርምጃ ነው። (ማቴዎስ 24:14) አንድ ሰው የይሖዋ አገልጋይ ሆኖ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ መርዳት መቻል እንዴት ያለ ታላቅ ደስታ ነው!— 1 ተሰሎንቄ 2:19, 20

